# ዲያብሎስን አገልጋይ ቀሳውስትና ካህናት

ዳግማዊ ጉዱ ካሣ - አዲስ አበባ(18/01/05)

**ትንሽ ምክር በተለይ ለኦርቶዶክሳውያን ምዕመናን**

ማሳሰቢያ፡- አክራሪ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ሰው (ካህንም ይሁን ምዕመን) ይህን ጽሑፍ እንዳያነብብ ይመከራል፡፡ ይህን ጽሑፍ የሃይማኖት ልዩነትን ለማራገብ የሚጠቀምበት ቢኖር የተንኮለኝነቱ መዘዝ የሚያስከትለው የእሳት ወላፈን እንዲፈጀው ከወዲሁ እጸልያለሁ፡፡

አንድ ነገር ከሰማሁ አያስችለኝም፡፡ የሰማሁትን ተንተርሼ የሚሰማኝ ባገኝ ከሚል እሳቤ በተለይ ለየዋሃንና ሰውን በቀላሉ ለሚያምኑ ዜጎች ይጠቅም ይሆናል ብዬ የምገምተውን በምክር መልክ ማስተጋባት ደስ ይለኛል፤ በአንድ ምክር አንድን ሰው ማዳን ከተቻለ ቀላል አይደለም፡፡ ‹ምክር የድሃ ነበርሽ ማን ቢሰማሽ› እንዲሉ ሆኖ ግን አላጋጩ በዛና የክራችንን ስናወራ የሚያምነን ጠፋ፡፡

በኦርቶዶክስ ሃይማኖት አንድ ምዕመን የንስሃ አባት ወይም የነፍስ አባት ይይዛል፡፡ ከጥንት ሲወርድ ሲወራረድ የመጣው ሃይማኖታዊ ትውፊታችን እንደሚያዘው አንድ ጨዋ ወይም ያልተማረ ምዕመን ብቻም ሳይሆን ማንኛውም የእምነቱ ተከታይ - ካህንም ሳይቀር - የነፍስ አባት መያዝ አለበት፡፡ ይህ የነፍስ አባት ሥልጣነ ክህነት ያለውና በመኖሪያ ቤትም እየሄደ ቡራኬ የሚሰጥ፣ ጠበል የሚረጭና የነፍስ ልጁን ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚያዘጋጅ የሥጋ ሳይሆን የነፍስ ጠበቃ ማለት ነው፡፡

ይህ ሰው በምዕመናን ዘንድ ከእግዚአብሔር ቀጥሎ እጅግ የሚከበርና የሚፈራም ነው፡፡ ምክንያቱም ክርስቶስ ለቅዱስ ጴጥሮስ ቃል በገባለት መሠረት “አንተ በምድር ያሰርካቸው በሰማይም የታሰሩ ናቸው፤ በምድር የፈታሃቸው ደግሞ በሰማይም የተፈቱ ናቸው” ስለሚልና ይህም ቃለ ወንጌል በሕዝቡ ዘንድ እንዲሠርፅ በመደረጉ በተለይ በትምህርት ብዙ ያልገፉ ወገኖች አንድን ቄስ ወይም እግዚአብሄርን አገልጋይ ካህን በጣም ያከብራሉ፤ ሌላው ቀርቶ እነዚህ ካህናት ወንጀልና ኃጢያት የሚሠሩ እንኳን አይመስላቸውም፡፡ በዚህ የዋህነት ግን እጅግ ብዙዎች ተታለዋል፤ ተጎድተዋልም፤ የፈረሱ ቤቶችና ትዳሮችንም ቤቱ ይቁጠራቸው፡፡ እኔ የማውቃቸው ጉዳዮች ራሳቸው አሁን እዚህ ብናገራቸው አውለው ያሳድራሉ፡፡ ሰው ግን በግልጽ ሲያወራ አይደመጥም - በሀፍረትና በይሉኝታ ገመዶች ተተብትቦ ይመስለኛል፡፡ ግን ነውር ነው፡፡ ከራስ በላይ ንፋስ በመሆኑ እውነትን በመነጋገር ቅሌታምን በማሳፈር ዋልጌነቱን እንዲተው ወይም ከዚያ በመጀመሪያ ተቀድሶ ኋላ ላይ በዲያብሎስ ምርኮኞች ከረከሰ ሥፍራ እንዲገለል ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ይህን ባለማድረጋችንም ይመስለኛል ቤተ መንግሥትም ቤተ ሃይማኖትም የጥንብ አንሣና የጭልፊት እንደልብ መናኸሪያ የሆኑብን፡፡

እንደእውነቱ ማመን እግዚአብሔርን ነው፡፡ ሰው ምን ጊዜም ሰው ነው - ሁለት እግራ አይታመንም ይባላል - የሰውን ያለመታመን አበሳ በሾርኒ ለማጣቀስ፡፡ እርግጥ ነው ከሰው ወገን የሚታመን ከነጭራሹ የለም ለማለትም አይደለም፡፡ ነገር ግን የማይታመነው ሞጭላፋ ይበዛልና ቢያንስ ባነሳሁት ነጥብ ዙሪያ ይህን ምክሬን ሰምታችሁ የበኩላችሁን ጥንቃቄ እንድታደርጉ ችግሮቹን ከነመፍትሔያቸው በመጠኑ ልጠቁም እሞክራለሁ፡፡ አንዱ ባንዱ እየሳቀ ጀምበር መግባቷ ይቅር፤ ነፍስ ዕንወቅና ጠላት ወዳጆችንን፣ ጎጂ ጠቃሚያችንን እንረዳ፡፡ በይትበሃልና በዘልማድ መጓዛችን ለከፋ ድህነትና ጉዳት ይዳርገናል እንጂ በምንም መንገድ አያሻሽለንም፤ ይቀብረናል ይልቁንስ፤ በአንጻራዊ ሁኔታ ከሌሎች ሀገራት ሕዝቦች ሳይቀር የተሻልን የነበርን ሕዝብ ዛሬ እንዲህ መሳቂያና መዘባበቻ ልንሆን የበቃነው ከኋላ ቀር ልማዶችና አሠራሮች ጋር ባለን የጠበቀ ቁርኝት ምክንያት እንደሆነ ብዙ ተጨባጭ ማስረጃዎችን በማጣቀስ መናገር ይቻላል፡፡ ከአንድ ማኅበረሰብ ጠላት መባቀያዎች ውስጥ በተገቢ ሰዎች የማይያዙ የሃይማኖት ተቋማት ዋናዎቹ ናቸው - ጫፍ ላይ የተበላሸ ነገር ግርጌም ላይ የመበላሸት ዕድሉ የሰፋ ነው፡፡ መለስ ዜናዊ ሥልጣን ከመያዙ አጎቱን አምጥቶ አምስት ኪሎ ላይ የጎለተው ለምን እንደሆነ የማይገባው ቢኖር ሰው ነኝ ባይል ይሻለዋል፡፡

ሰሞኑን ከተፈጸመ አንድ አሳዛኝ ነገር ልነሳ፡፡ አንድ ሰው ቤት ውስጥ አንድ ቄስ አዘውትሮ ይመላለሳል፡፡ ሰበቡ የዚያ ቤት የሚስትዮዋ አበ ነፍስ ሆኖ ነው - ባልዮው ሃይማኖቱ ሌላ ስለሆነ በመቻቻል የሰውዬውን መመላለስ ከጉዳይ ሳይጥፍ ይኖር ነበር፡፡ በቅርቡ ግን አንድ ነገር ተከሰተ፡፡ ባል መኪናውን አስነስቶ ከቤቱ ይወጣል፡፡ ሁነኛ ሰው ግን፣ የባልን እግር ተከትሎ የቄሱን ወደቤት መግባት ይጠቁመዋል፡፡ ባል ይመለሳል፡፡ የመኪና ድምጽ የሰሙ ሚስትና ቄስ ሁለተኛ ፎቅ ላይ ከሚገኘው መኝታ ቤት ሲወርዱ የፎቁ መውረጃ ደረጃ ላይ ከባል ጋር ይገጣጠማሉ፡፡ ያኔ ባል በያዘው ሌባ ጎማ የመሰለ ብረት ቄሱን አናቱን በርቁሶ ይጥለዋል፤ ሚስት የለበሰቻትን ስስ የመኝታ ቀሚስ እንደለበሰች ሮጣ ታመልጣለች፡፡ ዕዳ ከሜዳ ነውና ባል በአሁኑ ሰዓት ያን ቅንዝረኛ ቄስ በሆስፒታል እያሳከመ ይገኛል - ጨርሶት ቢሆን በተሻለ፡፡ ምናባቱ - ውሉደ አጋንንት ቢሞት ፍስሐና ሃሤት እንጂ የምን ሀዘን ነው!

እውነቱንና እውነቱን እንነጋገር ከተባለ እጅግ ብዙ ቄሶች ባለጌዎች ናቸው፡፡ ሰይጣናት ናቸው ማለትም ይቀላል፡፡ ራሳቸው ተዋርደው ሃይማኖታችንን እያዋረዱ ሕዝበ ክርስቲያንን እያሸፈቱት ናቸው - በአካልም በመንፈስም፡፡ ከላይ ከአናት ጀምሮ የተጣባቸው የሸርሙጥናና የቅንዝረኝነት አባዜ ቤተ ክርስቲያንን ሊያዘጋ የቀረው ጊዜ በጣም አጭር ነው፡፡ እግዚአብሔር ቤቱን ሊያጸዳ የሚነሳበት ጊዜ የሚኖረው ይመስለኛል፡፡ ያኔ ቤተ ክርስቲያንን እንደፍጥርጥሩ ያጽዳትና ንፋሽና ገለባውን በእሳት ያንድደው እንጂ አሁን እንደምናየው ከሞላ ጎደል ሁሉም ማለት በሚቻል ሁኔታ ካህናቱ በዘረኝነት ልክፍት የተጀቦኑ፣ በገንዘብ ፍቅር የታወሩ፣ በወሲብ ጥማት የተቃጠሉ፣ በቃለ እግዚአብሔር ባዶ ስብከት እንደቁራ ከመጮህ ውጪ አንዳችም ሃይማኖታዊ ፋይዳ የሌላቸው እርጉማን ሆነዋል፡፡ የዚህ ንግግሬን ኃጢያት እኔው እሸከማለሁና ማንም ከንፈሩን እንዲመጥልኝ አልሻም፡፡ የነሱን ወንጀል እንዳናወራና መነጋገሪያ

እንዳናደርጋቸው በተለያዩ ማስጠንቀቂያዎች አስቀድመው ያስሩናል - ሴቶችን በተለይ የለዩላቸው ባሪያዎቻቸው አድርገዋቸዋል፤ ከዚህ ነጥብ አንጻር በካቶሊክም ሆነ በሌላው እምነት ዘንድ ልዩነት የለም - በአንዴ ጠላት ማብዛቴ ጥሩ አይደለም እንጂ፡፡ ዳሩ እኔ ምን ቸገረኝ - ዋናው ነገር ከእመት እውነት ጋር አልጣላ፡፡ እውነት ደግሞ እውነት ናት፤ እኔ እንጂ እርሷ አትሞትም - ስለርሷ የሚሞት ደግሞ ይድናል፡፡ ካህናቱ እኛ ወደ እውነት እንዳንጠጋና  እንዲያውም እንድንሸሻት ሲፈልጉ ‹የምንለውን እንጂ የምናደርገውን አትከተሉ› ይሉናል፡፡ ሲያሻቸው ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል እየጠቀሱ ‹በራስህ ዐይን ውስጥ  ያለውን እርፍ እሚያህል ጉድፍ ሳታወጣ በጓደኛህ ዐይን ውስጥ የምትገኘውን መርፌ እምታህል  ጉድፍ ለማውጣት አትሞክር› ይሉናል፡፡ ምን አለፋችሁ አጭበርባሪዎች ናቸው፡፡ በነገራችን ላይ እኔ የማንኛውም ሃይማኖት ተጻራሪም ሆነ ጭፍን ደጋፊ አይደለሁም፡፡ ፍረጃ አያዋጣም፡፡ እውነት ደግሞ በፍረጃ (labeling) ተድበስብሳ ልትታለፍ አትችልም፡፡ ዓለም ለይቶላት መጥፋት የጀመረችው ፍረጃ ነፍስ ዘርቶ እንደዘመናችን ሰዎች በዘርና በሃይማኖት በሺዎች ቦታወች መከፋፈል ከጀመሩ ወዲህ ነው ቢባል ስህተት አይመስለኝም፡፡...

እውነቱን ነው የምላችሁ - ስንቶች የአበ ነፍስ ሰለባ አባዎራዎች በሚስቶቻቸው ላይ በነዚሁ የዲያብሎስ ልዑካን ካህናትና ቀሳውስት ምን የመሰለ የወሲብ ሻጥር እንደሚሠራና የትኞቹ ወይም የትኛው ልጅ የነሱ እንደሆነ አያውቁም፡፡ እነኚህ ጉግማንጉጎች ቤተ ክርስቲያናችንን የሰይጣን ማደሪያ አድርገው የማይሠሩት ሥራ የለም፡፡ መተተኞች፣ ሟርተኞች፣ መጣፍ ገላጮች፣ ጋንኤል ጎታቾች፣ ደንቃራ ጣዮች፣ አንደርብ ሠሪዎች፣ ጥላ ወጊዎች፣ ዐውደ ነገሥትና ኮከብ ቆጣሪዎች፣... በመሆን ለሁለት ጌቶች ተገዝተው ሕዝብን የሚያወናብዱ፣ የሚያደኸዩ፣ የሚያነሱ የሚጥሉና አመፃን ዘርተው መቅሰፍትን የሚያፈሩ ካህናት ናቸው፡፡ እነዚህንና ሌሎች ዓለማዊ ወንጀሎችንና ሃይማኖታዊ ህፀፆችን የሚያመርቱ ካህናትና ደባትር የተሰገሰጉባት ቤተ ክርስቲያናችን ካልጸዳች ችግሮች አሳሳቢ በሆነ ሁኔታ እየተራቡ መሄዳቸው አያጠያይቅም - እዚህ ላይ ንጹሓን የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሊኖሩ ይችላሉና ይቅርታ መጠየቅ ይገባኛል፤ እናም በጎያው እግዚአብሔር ስም የነዚህን ወገኖቼን ይቅርታ በታላቅ ትህና እጠይቃለሁ፡፡

በየአብያተ ክርስቲያንና በየሰበካ ጉባኤው ምን እየተካሄደ እንደሆነ የማናውቅ አይደለንም፡፡ ግን የእግዚአብሔር ሠይፍ ከአፎቱ እስኪወጣና እውነተኛ ፍርዱን እስኪሰጥ መጠበቅ ስላለብን ነው በግልጽ መቃወምን ያልተዳፈርነው፡፡ እንዲህ በሕዝብ ፊት ያዋረዱት እግዚአብሔር ቋቱ ሲሞላ ምን እንደሚሠራ ደግሞ እናውቃለን፡፡ ያረከሷት ቤተ ክርስቲያን ስትከብር የነሱ ቦታ ግልጽ ነው፡፡

እንደመፍትሔ፡፡ ሃይማኖት መቀያየሩ ዋጋ የለውም፤ በሁሉም ሥፍራ ያው ነው፡፡ ምናልባት የማናውቀው ነገር የተለዬ ሊመስለንና የተሻለ እንደሚሆንም ልንገምት እንችል ይሆናል - ይሁንና ስልቻ ቀልቀሎ፣ ቀልቀሎ ስልቻ  ዓይነት ነው፡፡ የሰው ልጅ ነጣ ጠቆረ፣ ኦርቶዶክስ ሆነ ጴንጤ፣ ቡድሂዝም ውስጥ ገባ ሰለመ... ያው ነው፡፡ ስህተት የሰው ልጅ መለያ የተፈጥሮ ባሕርይ ነው - ደረጃው ይለያይ እንደሆነ እንጂ፡፡ ስለዚህ ብለን ወደመፍትሄ እንግባ፡፡ ስለዚህ በያለንበት ጸንተን ግንኙነታችንን ከእግዚአብሔር (አላህ፣ጦሳ፣ዋቃ፣ጎይታ፣ጎድ፣ ዲዮ...) ወይም እንደየቋንቋችንና እምነታችን በምንጠራው የሃይማኖት ጫፍ(entity) እንጥና፡፡ ሰውን ከማምለክ እንቆጠብ፤ ሰውን እያመለክን እንዳልሆነ አውቃለሁ - ማለት የፈለግሁት ከመጠን በላይ ሰውን እያመንን ገደል አንግባ፤ ማጣፊያ ለሚያጥረው ችግርም አንጋለጥ - የምናምነው ፈረስ በደንደሳችን ሲጥለን የመነሻችን ነገር አጠያያቂ ነው፡፡ ከወደቅን በኋላ ‹ሴትን ያመነ ጉም የዘገነ› ወይም ‹ዱሮም አዳምን ለፈተናና ለውድቀት የዳረገችው ሴት ናት› እያልን ዕድልንና የተፈጠርንባትን ዕለት አምርረን ከመራገም ወይም በግድያ ዘብጥያ ከመውረድ አስቀድሞ መጠንቀቅ፣ ቤትን ከፍቶ ሰውን ሌባ ላለማለትም ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ ከብልህ ሰው ይጠበቃል፡፡ እናም ካህናት የሚያስፈልጋቸውን ደመወዝ አንንፈጋቸው፤ ቤተ ክርስቲያንም መሄድና መጸለይ ካለብን እንሂድና እንጸልይ፡፡ በመሠረቱ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር መኝታ ቤታችንን ዘግተን ብንጸልይም ይሰማናል - ዋናው እንዴትና ስለምን መጸለይ እንደሚገባን ማወቁ ላይ ነው፤ እኔን በዋናነት ጨምሮ ብዙ ሰው የጸሎትን ኃይልና እንዴት እንደሚጸለይ ስለማወቁ እርግጠኛ መሆን የሚቻል አይመስለኝም፡፡ አሁን በሞቴ ‹ ድንግልዬ! እስከዛሬ ወር ሀመር መኪና ካላስገዛሽኝ ደጅሽን አልረግጥም!› ወይም ‹የቁልቢው ገብርኤል! ዋሴ ጠበቃየ - እስከዚህ ቀን ድረስ እገሌን ባፍ ጢሙ ከደፋህልኝ አንድ ኮበሌ ዐይጥ ስለት አስገባለሁ› ... የሚሉ በኢትዮጵያ ብቻ እንደሚገኙ የምንገምታቸው ስለቶች ተገቢ ናቸው ትላላችሁ? ስለዚህ የጸሎት አቀራረብና የስለት አሳሳል ኮርስ የሚያስፈልገን ብዙ ነን ማለት ነው፡፡ በጋራ ከመጸለይ አኳያ ኅብረታችን ለመሰናከያነት ከዋለ በተናጠልም ብንሞክረው ጥፋት አይመስለኝም፡፡ ችግራችን ፈርጀ ብዙ ነው፤ ፖለቲካው ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊውና ሃይማኖታዊውም ዕድሳትና ጥገና (overhauling) ያስፈልገዋል፤ በጥቂት ነገር ወይም በባዶ መኮፈሱ ለትዝብት ከመዳረግ ውጪ አልፈየደልንም፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ከአጋንንት ግዛት እስክትወጣ በአቢይ ትጋት ጸንተን የጌታችንን የመድሓኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምፅዓት በትግስት እንጠባበቅ - እኔ እንደማንኛውም የአዳምና የሔዋን ዘር ኃጢያተኛና አላዋቂ ብሆንም፣ የመጥምቁ ዮሐንስን የዐዋጅ ቃል ተውሼ ‹ንስሃ ግቡ፣ መንግሥተ ሰማይ ቀርባለችና!› ብየ የበኩሌን በገሃድ ብጮኽ ደስ ባለኝ - ከምልክቶች መፈጸም አንጻር ጊዜው ደርሷል ብቻ ሳይሆን በሴከንዶችና በደቂቃዎች ውስጥ የሚከናወንም እስኪመስለን ድረስ እጅግ ቀርቧል - የሰው ልጆች ግን ማስተዋልን የተነጠቅን እንመስላለን፡፡ በዓለም ዙሪያ የሚታየው ሼሼ ገዳሜና ቸበር ቻቻ የሚያመለክተውም ይህንኑ የአእምሮ መነጠቅን ነው፡፡ ብሎም ቢሆን  ይህ ሁሉ የሃይማኖት ክስረትና የአገልጋዮች በዲያብሎስ ወጥመድ ውስጥ ገብቶ ምዕመናንን በተኩላና ቀበሮ ማስነጠቅ የመጨረሻው መጀመሪያ ነውና ብዙም አንደናገጥ፡፡ ያልተባለ ነገር አልተፈጸመም፡፡ ከተባለውም የቀረ ነገር የለም፡፡ ከፍ ሲል እንደጠቆምኩት በዚህ ረገድ ልናገር ብል ውዬ አሳድራችኋለሁ፡፡ ለመሰነባበቻ ግን አንዲት ወደቀልድነት የዞረች እውነተኛ ገጠመኝ ልንገራችሁና ፈገግ ካደረገቻችሁ ፈገግ በሉ፡፡

አንድ የንስሃ ልጁን ሚስት የለመደ ቄስ ነበር፡፡ ንጋት ላይ አባወራውን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በወንዶች መግቢያ ገብቶ ቅዳሴ ሊከታተል መቆሙን ከውስጠኛው ከመቅደሱ ሆኖ  ያየዋል፡፡ ያኔ የርሱን የቅዳሴ ድርሻ እንዲሸፍንለት ላንዱ ካህን ጓደኛው ይሰጥና

በቅርብ ወደሚገኘው የንስሃ ልጁ ቤት ገብቶ የነፍስ ልጁን ሚስት ‹ይጠምዳል› - ሌላ ቅዳሴ፡፡ ይሄኔ ያ የዋህ ምዕመን በሆነ ሌላ አጋጣሚ ወደቤቱ የሚሄድበት ነገር ይከሰትና ቤቱን ከፍቶ ሲገባ ያ ቄስ ከመደቡ ተነስቶ በጓሮ በር ውልቅ ብሎ ሲወጣ ውልብ ይለዋል፡፡ በቤቱ እየሆነ ያለውን ነገር አምኖ ለመቀበልም ዐይኑን ማመን ያቅተዋል፡፡ ጉድ ብሎ የጀመረውን ቅዳሴ ሊጨርስ ወደቤተክርስቲያን ይመለሳል፡፡

ከማግሥቱ ጀምሮ ግን ያ ባል ፍቺ ይጠይቃል፡፡ የነገር አባቶች ሥርክ ይሰበሰቡ ያዙ፡፡ የፍቺው ምክንያት ያልተገለጠላቸው የንስሃ አባትም በየቤተ ዘመድ ጉባኤው እየተገኙ ‹ኧረ ተው ልጆቼ፣ የክርስቶስን ቅዱስ ጋብቻ አታርክሱ፤ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ማንም እኮ ሊለየው አይቻለውም› እያሉ ቢመክሩ ባል ወይ ፍንክች! ሴትዮዋ ስትጠየቅ ምንም የሚያፋታቸው ምክንያት እንዳልተፈጠረ፣ ትዳሯንም እንደምትወድ፣ ባሏ አንዳችም በደል እንደማያደርስባትና በትዳሯ ደስተኛ እንደሆነች ትገልጣለች፡፡ ሰውዬው ግን አፋቱኝ ብሎ ድርቅ ይላል፡፡ ባልዮው ፍቺን ብቻ ፈለገ እንጂ አንድም ምክንያት ባለማቅረቡ ሁሉም ተጨነቁ - ንስሃ አባት ሳይቀሩ፡፡

በመጨረሻው ግን በቀላሉ መገላገል ፈለገና ባልዮው የሆነ የውሸት ምክንያት ማቅረብን ወደደ፡፡ ‹ምክንያት አለኝ› ብሎ ጉሮሮውን ማሳላት ሲጀምር ቄሱም ሌሎቹ ሽማግሎችም በጉጉት አፋቸውን ከፍተው ማዳመጡን ተያያዙት፡፡ ባል ቀጠለ፡- ‹ምክንያት አለኝ፤ ምክንያቴ ሚስቴ ወይዘሮ አወጣሽ አልጋ ላይ ሡነፍ ናት…› ብሎ ከመጨረሱ ቄሱ በፍሩዲያን የምላስ ወለምታ ቅኝት ቀበል አደረጉና ‹ኧረግ! እንዝርት ናት!› አሉና ዐረፉት ይባላል - እንዴት እንዝርትነቷን እንዳወቁት የሽማግሎቹም ብቻ ሳይሆን የኛ የዚህን መጣጥፍ አንባቢዎችም ጭምር ጥያቄ ነው፡፡ ባልዮው ግን ብልጥ ነው - ያን ምክንያት የሰጠው ስንፈተ ወሲብ የፍቺን የወዲያው ጽድቅና ከሚያሰጡ ገመናዎች አንዱ መሆኑን ስላወቀ ወይም ስለተመከረ ነው፡፡ (ለጠቅላላ ዕውቀት - ሚስቴ ቀዘቀዘች ወይም ባሌ እንደግንዲላ ተጋድሞ እኔን ሳያቅፈኝ ያድራል የሚል የፍቺ ምክንያት ከቀረበ ማስረጃ አቅርቡ እማኝ ጥሩ ሳይባል ፍቺው በአንድ ጀምበር ይጸድቃል አሉ - የሕግ ዕውቀት ወይም ትምህርት ያላችሁ ደግፉኝ)፤ አይገርምም ትላላችሁ? የውስጡን ለቄስ ነገር እንግዲህ እንዲህ ነው፡፡ ቄስን ያመነ ጉድ ሆነ፡፡ ጎበዝ - ጠንቀቅ ነው ደጉ! እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን በቶሎ ይጎብኝልን፡፡ አሜን፡፡ ሌላ ጊዜ በልጅነቴ የገዛ አጎቴን እንዲሞት አስደርጎ የአጎቴን ሚስት (የ10 ልጆች እናት!) ገና ዐርባው ሳይደርስ ስላገባው የነፍስ አባት እነግራችኋለሁ፤በኔ ይሁንባችሁ ቅሌታምን ቅሌታም ማለት ነውር የለውም፡፡ የምን መደባበቅ ነው! በኛ ይብቃ - ትውልድ ይዳን ስንል በኤች አይ ቪ ኤድስ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ረገድ መሆን አለበት፡፡ ይህን መሰል ታሪክ የምታውቁ ሌሎች ወገኖችም ዝም አትበሉ፡፡ ደግሞም ስትናገሩ ከሃይማኖት ጦርነት አንጻር ማለትም አንዱን ከፍ ሌላውን ዝቅ ከማድረግ አኳያ ሳይሆን እውነትን ብቻ መስክሩ፡፡ ይሄ ከባልሽ ባሌ ይበልጣል ሽሮ አበድሪኝ ዓይነቱ የሃይማኖት ሽኩቻ ዋጋቢስ ነው፡፡ አይጠቅምም ብቻ ሳይሆን የሰውነትን ደረጃ ዝቅ የሚያደርግ ከንቱ ነገር ነው፡፡ የሚጸድቀው የሚታወቀው በሰው ሳይሆን በፈጣሪ ነው፡፡ ሆኖም ቢሆን መልካም ነገርን መሥራት ለሁሉም ዓይነተኛ መደላድል ነው፡፡ እየገደሉ፣ እየሰደቡ፣እየተቀራቀሱ፣ እየተጠላሉ፣ ለግድያና ለጥቃት እያደቡ፣እየተዛዛቱ… ኩነኔ እንጂ ጽድቅ ብሎ ነገር የለም፡፡ ውይ ሰው ግን! መጥኔ ለምድሪቷ …